# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# የማስተላለፊያ መስመሮችና ማከፋፈያ ጣቢያዎች ቴክኒካል ድጋፍ

ጥላሁን ጌታነህ

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በፈጠራ፣ በቴክኖሎጂ፣ በተሞክሮ፣ በፍትሃዊነት እና በቁርጠኝነት አስተማማኝ እና ዘላቂ ኃይልን የማቅረብ ተልዕኮ ይዞ በተሻሻለው የኢፌዴሪ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 381/2008 መሠረት የተቋቋመ የመንግሥት የልማት ድርጅት ነው። ተቋሙ ተልዕኮውን በብቃት ለመወጣትና የተጣለበትን ሀገራዊ ኃላፊነት ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉትን የሥራ ክፍሎች አዋቅሮ ወደሥራ ገብቷል። ከእነዚህ ክፍሎች ውስጥ በማስተላለፊያ መስመሮችና ማከፋፈያ ጣቢያዎች ኦፕሬሽን ዘርፍ የቴክኒካል ድጋፍ መምሪያ አንዱ ሲሆን እኛም የክፍሉ አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ ምን ይመስላል? ስንል ከመምሪያው ዳይሬክተር አቶ አበባው ያለው ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አቅርበናል። ቃለ ምልልሱን በክፍል አንድ እና በክፍል ሁለት ፕሮግራሞች የምናቀርብ ሲሆን ይህ የክፍል አንድ ዝግጅታችን ነው። መልካም ንባብ!

ኮርፖሬት ኮሙዩኒኬሽን፡- መምሪያው እንዲቋቋም ዋነኛ ምክንያቱ ምን ነበር?

አቶ አበባው፡- በትራንስሚሽን ሰብስቴሽን ቴክኒካል ድጋፍ መምሪያ የትራንስሚሽን ሰብስቴሽን አሴት ማኔጅሜንት ቢሮ እና የትራንስሚሽን ኦፕሬሽን ሲስተም ማሻሻያ ቢሮ የተባሉ ሁለት ክፍሎች ይዞ ከአንድ ዓመት በፊት ነው የተቋቋመው። መምሪያው እንዲቋቋም ያስፈለገበት ዋነኛ ምክንያት ተቋሙ ባሉት 13 አካባቢ ሪጅኖች የሚሰሩ የፍተሻና የጥገና ድንገተኛ ሥራዎች ወጥነት ያለው



አቶ አበባው ያለው

አሠራር በመቅረጽ ሥራቸውን በቴክኖሎጂ በመታገዝ እንዲያከናውኑ ለማስቻል ነው። እንዲሁም በዘርፉ ሥር ያሉትን ሀብቶች በመመዝገብና በቂ መለዋወጫ በማቅረብ ደህንነታቸውን በመጠበቅ አስተማማኝ የሆነ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትን ለማረጋገጥ ነው።

ኮርፖሬት ኮሙዩኒኬሽን፡- መምሪያው በሥሩ ባሉ የሥራ ክፍሎች አማካኝነት የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባርት ምንድን ናቸው?

አቶ አበባው፡- ቀደም ብዬ ለመግለጽ እንደሞከርኩት መምሪያው በሥሩ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን በርካታ ተግባራትንም ያከናውናል። ለአብነትም በትራንስሚሽን ሰብስቴሽን ኦፕሬሽን ስር ያሉ ሀብቶችን መመዝገብ፣ ደህንነታቸውን መከታተል፣ በቂ መለዋወጫ መኖሩን ማረጋገጥ፣ የመለዋወጫ ግዥን በማጥናት ግዢ እንዲፈጸም ማቅረብ፣ መድን የሚያስፈልጋቸውን ዕቃዎች በመለየት መድን እንዲገባላቸው ማቅረብ፣ የመድን ካሳ ክፍያን ማስፈጸም፣ ጉዳት የደረሰባቸውን ዕቃዎች በመለየት የመድን ክፍያቸው መፈጸሙን መከታተል፣ የአገልግሎት ደረጃ ስምምነት (Service Level Agreement- SLA) የውል ሰነዶችን ከመፈረማቸው በፊት መርምሮ ግብዓት መስጠትን ያከናውናል። በተጨማሪም ኦፕሬሽናል ፖሊሲ፣ አሠራር እና መመሪያ በማጥናት ማዘጋጀት፣ በቴክኒካል ችግር ምክንያት የአገልግሎት ዘመናቸው ሳይደርስ ብልሽት ያጋጠማቸውን የከፍተኛ መስመር እና የማከፋፈያ ጣቢያ እቃዎች በማጥናት የችግሩን መንስኤ በመለየት ድጋሚ እንዳይከሰት የመፍትሔ ሃሳብ ማቅረብ፣ የኤሌክትሪክ አቅርቦትን አስተማማኝ ለማድረግ ጥናትና ምርምር በማከናወን የመፍትሔ ሃሳብ ማቅረብም ይሠራል። በዘርፉ ሥር የሚከናወኑ ሁሉንም ተግባራት የጥራት አስተዳደር ሥርዓት( QMS)ን የተከተለና የተቋሙን የ-ISO 9001 ዓለም አቀፍ ደረጃን የተከተለ እንዲሆን ሥርዓቶችን፣ አሠራሮችን፣ ፖሊሲዎችን፣ ማኑዋሎችን ወዘተ በወጥነት ማጥናት፣ ትግበራን በመከታተል፣ የጥራት ኦዲት ሥራዎችን እና ለዘርፉ የሚመጡ ጥያቄዎችንም ዘርፉ በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት ይተገብራል።

ለኃይል ማስተላለፊያና ማከፋፈያ ጣቢያ ኦፕሬሽን ሥራ አስፈላጊ የሆኑ አሠራሮችን፣ ደረጃዎችንና ፖሊሲዎችን በማውጣትና በመለየት ተንትኖ በማጸደቅ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ያሳውቃል፤ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል። የጎደሉና በጊዜ ሂደት የተቀየሩ የማከፋፈያና የማስተላለፊያ መስመር ሰነዶችን ጥናት በማድረግ የማሟላት፣ በእርጅና ምክንያት የአገልግሎት ዘመናቸው የተጠናቀቁ የማስተላለፊያ መስመርና ማከፋፈያ ጣቢያ አሴቶችን በማጥናት እንዲሁም ከሪጅኖች በሚቀርበው ጥያቄ መሠረት በመገምገም የማሻሻያ፣ የአቅም ማሳደጊያ እና የከፍተኛ ጥገና ፕሮፖዛል የማቅረብ ተግባራትንም ያከናውናል።

ኮርፖሬት ኮሙዩኒኬሽን፡- መምሪያው በምን በምን ጉዳዮች ላይ የቴክኒካል ድጋፍ እንደሚደረግ ቢገልፁልን?

አቶ አበባው፡- መምሪያው የቴክኒክ ድጋፍ የሚያደርገው የተበላሹ ዕቃዎች የብልሽታቸውን ምክንያት በማጥናት ብልሽቱ እንዳይደገም የማድረግ ሥራ በመሥራት እና ማሻሻያ የሚፈልጉ መስመሮችና ማከፋፈያ ጣቢያዎችን በማጥናት ማሻሻያ በማድረግ ነው። ጉዳት የደረሰባቸውን ዕቃዎች በመለየት የመድን ክፍያቸው እንዲፈጸም የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በማሟላት፣ ለትራንስሚሽን ሰብስቴሽን ኦፕሬሽን ሥራ አስፈላጊ የሆኑ አሠራሮችን፣ ደረጃዎችን፣ ፖሊሲዎችን በማውጣት፣ የPSLA የውል ሰነዶችን ከመፈረማቸው በፊት በመመርመርም ድጋፍ ያደርጋል። በተጨማሪም በማስተላለፊያ መስመርና ማከፋፈያ ጣቢያዎች ኦፕሬሽን ስር ያሉ ሀብቶችን እንዲመዘገቡ ፎርማት በመቅረጽና ደህንነታቸውን በመከታተል፣ በቂ መለዋወጫ መኖሩን በማረጋገጥ፣ የመለዋወጫ ግዥን በማጥናት ግዢ እንዲፈጸም በማሳወቅ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል።

ውድ አንባቢዎች የክፍል አንድ ዝግጅታችን በዚህ አበቃ። በቀጣይ በክፍል ሁለት ዝግጅት እስከምንገናኝ መልካም ሳምንት ይሁን ብለን ተሰናበትን!

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ